# አጥፍተህ ተቀደስ

ኢትዮጵያዊው ሁሉ ፤ ታሪኩን ሲያዋሳ
እንዳልተጀነነ ፤ እንደ ዳልጋ አንበሳ
ባገሩ እንዳልኮራ ፤ በምኒሊክ ካሳ
ቀን ስለዘመመ ፤ ታሪክ አይረሳ !
ዛሬ ስልጣን ገብቶ ፤ ባናሶች አናሳ
መኘገር ሆነውበት ፤ የሀገር ነቀርሳ
ባገሩ እንዴት ይፈር ፤ በባንዳ የተነሳ ።

ዘመን አረጀና ፤ ጊዜው ተለውጦ
የትግሬ ወያኔ ፤ ዛሬ አለልክ አብጦ
ለባዕድ ተቀጥሮ ፤ ጥርሶቹን አግጥጦ
ህዝብ እያስለቀሰ ፤ ሲገዛ ቀጥቅጦ
ኢትዮጵያን ሲያጠፉት ፤ ሲበላት ጋግጦ
አገር ድንበር ሲንድ ፤ ከላይ ተፈናጦ
ጀግናው ወዴት ገባ ፤ አይነሳ አምጦ?
ምን አንጀት ቢኖረው ፤ ያያል ተቀምጦ ።

በጎሳና በጎጥ ፤ ሸንሽኖ አገር ሲያፈርስ
የባንዳ ጥርቅም ፤ ባገር ሲልከሰከስ
ጥርስ እየነከሱ ፤ በቁጭት ከማልቀስ
ከነ ግሳንግሱ ፤ ሁለተኛ እንዳይደርስ
ይህን የንግዴ ልጅ ፤ አጥፍተህ ተቀደስ
ኢትዮጵያም ትኩራብህ ፤ ስራና ተወደስ ።

ታዛቢው … April 21, 2010